
ETHIOPIAN AGRICULTURAL BUSINESSES CORPORATION
ETHIOPIAN AGRICULTURAL BUSINESSES CORPORATION

# የኢትዮጵያ የግብርና ሥራዎች ኮርፖሬሽን

# የዜጎች ቻርተር

የኢትዮጵያ የግብርና ሥራዎች ኮርፖሬሽን
ETHIOPIAN AGRICULTURAL BUSINESSES CORPORATION

# ማውጫ

## ርዕስ


ክፍል አንድ

1. ጠቅላላ ገጽ
1.1 መግቢያ ........................................................................1
1.2 ትርጓሜ ........................................................................2
1.3 የሕግ መሠረት ................................................................2
1.4 የተቋሙ ሥም .................................................................2
1.5 ቻርተሩ የተዘጋጀበት ጊዜ ...................................................3
1.6 የቻርተሩ ዓላማ ...............................................................3
1.7 የቻርተሩ አስፈላጊነት ........................................................3

ክፍል ሁለት

2. ተልዕኮ፣ ራዕይ፣ ዕሴቶች፣ ደንበኞች፣ ባለድርሻ አካላት እና የጥራት መርሆዎች
2.1 የኮርፖሬሽኑ ተልዕኮ፣ ራዕይ እና እሴቶች ....................................4
2.2 የኮርፖሬሽኑ ደንበኞችና ባለድርሻ አካላት .....................................4
2.3 አጠቃላይ የጥራት መርሆዎች .................................................5

ክፍል ሦስት

3. ተግባርና ኃላፊነት፣ አገልግሎቶች፣ መብት፣ ግዴታ፣ ቅሬታ መቀበያና ማስተላለፊያ ዘዴዎች
3.1 የኮርፖሬሽኑ ተግባርና ኃላፊነት ..............................................6
3.2 በኮርፖሬሽኑ የሚቀርቡ የግብርና ግብዓቶች እና አገልግሎቶች...........6
3.3 የኮርፖሬሽኑ የሥራ ዘርፎች ምርት እና አገልግሎቶች ......................7
3.4 የደንበኞች መብቶች ..........................................................9
3.5 የኮርፖሬሽኑ ግዴታዎች ......................................................10
3.6 የኮርፖሬሽኑ ሠራተኞች ለደንበኞች የገቡት ቃል .........................10
3.7 አስተያየትና ቅሬታ መቀበያ ዘዴዎች .........................................10
3.8 የመረጃ ማስተላለፊያ ዘዴዎች ................. ..............................11

ክፍል አራት

4. የቻርተሩ አተገባበር ሂደት
4.1 የቅሬታ አቀራረብ ሥርዓት ...................................................12
4.2 የክትትልና ግምገማ ሥርዓት .................................................13
4.3 ተጠያቂነት .....................................................................13
4.4 የዜጐች ቻርተሩን በሥራ ላይ ስለማዋል ......................................14
4.5 የዜጐች ቻርተሩን ስለማሻሻል .................................................14

ክፍል አምስት

5. የአቅርቦት እና የአገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርድ .............................15

ክፍል ስድስት

6. ተቋማዊ መዋቅር ................................................................22

# ክፍል አንድ

## 1.1 መግቢያ

የኢትዮጵያ የግብርና ሥራዎች ኮርፖሬሽን (ኢግሥኮ) በግብርናው ዘርፍ ከ30 እስከ 40 ዓመት ድረስ በተናጠል አገልግሎት ሲሰጡ የቆዩ አምስት ነባር ድርጅቶችን (የኢትዮጵያ ምርጥ ዘር ድርጅት፣ የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት፣ የእርሻ መሣሪያዎችና የቴክኒክ አገልግሎት አክሲዮን ማኅበር፣ የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት ድርጅት እና የተፈጥሮ ሙጫ ምርትና ገበያ ልማት ድርጅት) በማዋሃድ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 368/2008 መሠረት ታህሳስ 2008 ዓ.ም የተቋቋመ መንግሥታዊ የልማት ድርጅት ነው፡፡

በግሉ ዘርፍና በተደራጁ ማኅበራት የማይሸፈኑ የገበያ ክፍተቶች ውስጥ የድርሻውን በመውሰድ ዘርፈ ብዙ ተግባራትን በማከናወን ላይ የሚገኘው ኮርፖሬሽኑ ተጠሪነቱ ለኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስ ሲሆን፣ በሥራ አመራር ቦርድ ይመራል፡፡

የተቋቋመበት ዓላማ ለግብርና ምርትና ምርታማነት ዕድገት አስተዋጽኦ የሚያደርጉ እና ለዘመናዊ እርሻና ለአግሮ ኢንዱስትሪ መስፋፋት መሠረት የሚሆኑ ቴክኖሎጂዎችን እና ግብዓቶችን በተመጣጣኝ ዋጋ ተደራሽ በማድረግ ሀገራዊ ልማትና ዕድገትን ለማፋጠን ነው፡፡

ኮርፖሬሽኑ ሀገራችን ለነደፈችው ሰፊ የግብርና ልማት ሥራዎች ተግባራዊነት የበኩሉን ኃላፊነት እንዲወጣ በተሰጠው ኃላፊነት መሠረት የሚያቀርባቸውን ምርቶች እና የሚሰጣቸውን አገልግሎቶች ደንበኞች በቅድሚያ ተረድተው በምን መልክ ማግኘት እንደሚችሉ ለማስገንዘብ እንዲሁም ማሟላት የሚገባቸውን ቅድመ ሁኔታዎችና መስፈርቶች አስቀድሞ ለማሳወቅ የዜጐች ቻርተር አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በተጨማሪም ኮርፖሬሽኑ ባስቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት ደንበኞች ተገቢውን ግብዓት እንዲሁም አገልግሎት ካላገኙ አስተያየት፣ ቅሬታ፣ ምስጋና እና ጥቆማ ሲኖራቸው በምን አግባብ ማቅረብ እና ምላሽ ማግኘት እንደሚችሉ ለማሳወቅ ቻርተሩ ጠቀሜታ አለው፡፡ ከዚህ ባሻገር ከባለድርሻ አካላት ጋር በልማትና መልካም አስተዳደር ጉዳዮች ዙሪያ የጋራ መግባቢያ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል፡፡

ቻርተሩ ኮርፖሬሽኑ በማቋቋሚያ ደንቡ የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት ለመወጣት እና በሀገራችን የለውጥ ሥራዎች ውስጥ ትርጉም ያለው አስተዋጽኦ ለማበርከት

በአደረጃጀት፣ በሰው ኃይል፣ በአሠራር እና መመሪያዎች እራሱን በማጠናከር የደንበኞችን ፍላጎት ለማርካት የተዘጋጀ ሲሆን፣ ደንበኞችም የሚጠበቅባቸውን ግዴታዎች በማሟላት የምርት እና የአገልግሎታችን ተጠቃሚ እንደሚሆኑ ይታመናል፡፡

በአጠቃላይ የኢትዮጵያ የግብርና ሥራዎች ኮርፖሬሽን የዜጎች ቻርተር የተዘጋጀው በቀጣይ ዘርፎች፣ ሥራ አመራሮች፣ መምሪያዎች፣ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች እና ጣቢያዎች የሥራ ክፍሎቻቸውን ዝርዝር ስታንዳርድ እና የዜጎች ቻርተር እንደሚያዘጋጁ ታሳቢ ተደርጎ ነው፡፡ ይህ ቻርተር የኮርፖሬሽኑን ተልዕኮ፣ ራዕይ፣ እሴት፣ የቻርተሩን ዓላማ፣ ኮርፖሬሽኑ የሚያቀርባቸውን ምርት፣ የሚሰጣቸውን አገልግሎቶች፣ ተጠቃሚ ደንበኞችን፣ አገልግሎት የሚሰጥባቸውን የሥራ ክፍሎች እና ቦታዎች፣ አገልግሎት ለማግኘት የሚፈጀው የጊዜ ስታንዳርድ እንዲሁም የመረጃ ማሰራጫ መንገዶችን እና የኮርፖሬሽኑን የሥራ ዘርፎች አድራሻዎች በማካተት የተዘጋጀ ሠነድ ነው፡፡

## 1.2 ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ሰነድ ውስጥ የዜጎች ቻርተር ማለት ደንበኞች በኮርፖሬሽኑ ማግኘት ስለሚችሉት ምርት እና አገልግሎቶች፣ የአገልግሎት አሰጣጥ የጊዜ ስታንዳርድ፣ ከጥራት እና ከወጪ አንጻር በግልጽነት መርህ ቀድሞ የሚያሳውቅና ይኸው አገልግሎት በተጓደለ ጊዜም መብታቸውን ለማስከበር አቤቱታ እና ቅሬታ የሚያቀርቡበትን ሂደት በአጭር፣ በግልጽና በቀላል ቋንቋ የሚገለጽበት ሰነድ ነው፡፡

## 1.3 የሕግ መሰረት

የዜጎች ቻርተር በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 12 (ቁጥር 1 እና 2) እንዲሁም በኮርፖሬሽኑ የሥራ መሪዎች መተደደሪያ መመሪያ እና በኀብረት ስምምነቱ መሰረት ተፈጻሚ እንዲሆን የተዘጋጀ ነው፡፡

## 1.4 የተቋሙ ስም

የኢትዮጵያ የግብርና ሥራዎች ኮርፖሬሽን ነው፡፡

## 1.5 ቻርተሩ የተዘጋጀበት ጊዜ

ቻርተሩ በ2009 ዓ.ም የተዘጋጀ ሲሆን፣ በ2017 ዓ.ም ማሻሻያዎች ተደርጐበት እንደገና ታትሟል።

## 1.6 የቻርተሩ ዓላማ

በሀገራችን እየተመዘገበ ያለው ፈጣን እና ዘላቂ የኢኮኖሚ ዕድገት በዳበረ ልማታዊ አስተሳሰብ እና የተወዳዳሪነት መንፈስ የተቀላጠፈ፣ ግልፅና ተጠያቂነት ባለው አሠራር ምርት እና አገልግሎቶችን ለተጠቃሚዎች ተደራሽ በማድረግ የደንበኞችን እና የባለድርሻ አካላትን እርካታ ወደ ላቀ ደረጃ ለማድረስ ሲሆን፣ የሚከተሉት ዓላማዎች አሉት።

- ለደንበኞች ጥራት ያላቸውን የግብርና ግብዓቶች ለማቅረብና የተቀላጠፈ አገልግሎቶችን ለመስጠት፣
- የደንበኞች እና የባለድርሻ አካላትን መረጃ የማግኘት መብት ለማረጋገጥ፣
- ግልፅነት እና ተጠያቂነት ያለው አሠራር ለማስፈን፣
- ቀልጣፋ እና ፍትሐዊ አሠራር ለመዘርጋት፣
- ደንበኞች ምን አይነት ምርት እና አገልግሎት በምን የጥራት ደረጃ ማግኘት እንደሚችሉ እና የሚወስደውን ጊዜ ለማሳወቅ፣
- ደንበኞች በሚቀርበው ምርት እና አገልግሎት ላይ ባላቸው እርካታ ዙሪያ አስተያየት፣ ጥቆማ እና የማሻሻያ ሀሳብ የሚሰጡበትን ሁኔታ ለማመቻቸት ነው።

## 1.7 የቻርተሩ አስፈላጊነት

- ቻርተሩ ደንበኞች ከኮርፖሬሽኑ ማግኘት ስለሚችሉት የግብርና ግብዓቶች እና አገልግሎቶች፣ የአገልግሎት ደረጃ በጊዜ፣ በመጠን፣ በጥራት፣ በግልፅነት መርህ ቀድሞ የሚያሳውቅ እና ይህ በተጓደለ ጊዜ መብታቸውን ለማስከበር አቤቱታ እና ቅሬታ የሚያቀርቡበትን ሂደት በአጭር፣ በግልጽና ገላጭ በሆነ ቋንቋ ለደንበኞች ያሳውቃል።

- ከባለድርሻ አካላት ጋር በልማትና መልካም አስተዳደር ጉዳዮች ዙሪያ የጋራ መግባቢያ ሊሆን የሚችል ሰነድ በማስቀመጥ አፈጻጸሙን ተከትሎ ለሚነሱ ጥያቄዎች ትክክለኛ ምላሽ ለመስጠት ያስችላል።

# ክፍል ሁለት

## 2.1 የኮርፖሬሽኑ ተልዕኮ፣ ራዕይ እና እሴቶች

### ተልዕኮ

ለግብርና ምርትና ምርታማነት ዕድገት አስተዋጽዖ የሚያደርጉ፣ ለዘመናዊ እርሻና ለአግሮ ኢንዱስትሪ መስፋፋት መሠረት የሚሆኑ ቴክኖሎጂዎችን እና ግብዓቶችን ተደራሽ በማድረግና በተመጣጣኝ ዋጋ በማቅረብ ሀገራዊ ልማትና ዕድገትን ማፋጠን፡፡

### ራዕይ

በግብርና ግብዓት አቅርቦት እና በሜካናይዜሽን አገልግሎት በ2022 ዓ.ም በአፍሪካ ተወዳዳሪ ተቋም መሆን፡፡

### እሴቶች

- ተዓማኒነት
- ግልጽነት
- ቅንነት
- ቁርጠኝነት
- የጋራ ተጠቃሚነት
- ማኅበራዊ ኃላፊነት

## 2.2 የኮርፖሬሽኑ ደንበኞች እና ባለድርሻ አካላት

### 2.2.1 ደንበኞች

- አርሶ አደሮች፣ ከፊል አርሶ አደሮችና አርብቶ አደሮች
- ክልሎች እና የኅብረት ሥራ ማኅበራትና ዩኒየኖች፣
- ሰፋፊ የመንግሥት እና የግል እርሻዎች፣
- የግብርና ኮሌጆች፣
- የክልል ምርጥ ዘር ኢንተርፕራይዞች፣
- በግብርና ዘርፍ ላይ የተሰማሩ ባለሃብቶች፣

- የተፈጥሮ ሙጫና የደን ውጤት ተጠቃሚ ድርጅቶች፣
- ሌሎች መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች (የሀገር ውስጥና የውጭ)፣
- ሚዲያ (መገናኛ ብዙሃን)፣

## 2.2.2 ዋና ዋና ባለድርሻ አካላት

- የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስ፣
- የኮርፖሬሽኑ የሥራ አመራር ቦርድ፣
- የሠራተኛ ማኀበር፣
- ሠራተኛ፣
- የፋይናንስ ተቋማት (ባንክና ኢንሹራንስ)፣
- የግብርና ሚኒስቴር፣
- የገቢዎች ሚኒስቴር፣
- የክልል ቢሮዎች፣
- የግብርና ግብዓት አቅራቢዎች፣
- የምርጥ ዘር ኢንተርፕራይዞች፣
- የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር፣
- የግል ዘር አባዥዎች፣

## 2.3 አጠቃላይ የጥራት መርሆዎች

- ጥራታቸውን የጠበቁ የግብርና ግብዓቶችን እና አገልግሎቶችን እናቀርባለን፣
- ከስህተት የፀዳ አገልግሎት እንሰጣለን፣
- በትህትና አገልግሎት እንሰጣለን፣
- ሁሌም ለመማርና ለማሻሻል እንተጋለን፣
- ላስቀመጥናቸው እሴቶች እንገዛለን፣
- ሁሌም ለጥራት መሻሻል እንተጋለን፣
- ለደንበኞች ጥያቄዎች እና አስተያየቶች ፈጣን ምላሽ እንሰጣለን፣
- ለሰጠናቸው አገልግሎቶችና ለወሰናቸው ውሳኔዎች ተጠያቂዎች ነን፣
- በመረጃ ላይ የተመሰረተ የውሳኔ አሰጣጥ ሥርዓት እናሰፍናለን፣
- የለውጥ መሣሪያዎችን ተግባራዊ በማድረግ የአገልግሎት አሰጣጣችንን ጥራት እናሻሽላለን::

# ክፍል ሦስት

## 3. ተግባርና ኃላፊነት፣ አገልግሎቶች፣ መብት፣ ግዴታ፣ ቅሬታ መቀበያና ማስተላለፊያ ዘዴዎች

## 3.1 የኮርፖሬሽኑ ተግባርና ኃላፊነት

የኢትዮጵያ የግብርና ሥራዎች ኮርፖሬሽን ዐበይት ተግባራት እና ኃላፊነቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

- የግብርና ምርት ማሳደጊያዎችን በማምረት እና በሀገር ውስጥና ከውጭ ሀገር ገዝቶ ለገበያ ማቅረብ፣ ማዘጋጀት እና የገበያ ዋጋ የማረጋጋት ተግባራትን ማከናወን፣
- የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት፣ የእርሻና የኮንስትራክሽን መሣሪያዎች የጥገና አገልግሎት፣ የእርሻ መሣሪያዎችና የትራንስፖርት ተሽከርካሪዎች የኪራይ አገልግሎት በክፍያ መስጠት፣
- የእርሻ መሣሪያዎችንና መለዋወጫዎችን፣ የኮንስትራክሽን መሣሪያዎችን እና አግሮ ኬሚካሎችን ከሀገር ውስጥና ከውጭ ሀገር ገዝቶ ለሽያጭ ማቅረብ፣
- የተፈጥሮ ሙጫ መሰብሰብ፣ መግዛት፣ እሴት መጨመር፣ ማዘጋጀት፣ ሌሎች ከደን ውጤቶች የሚመረቱ ምርቶችን (እጣን፣ ከርቤና አበከድ) ማምረት፣ ለሀገር ውስጥና ለውጭ ገበያ ማቅረብ፣
- የእርሻ መሬት ልማት ጥናትና ዲዛይን፣ የእርሻ መሬት ቅየሳ ምንጣሮ እና ማስተካከል፣ የውኃ ተፋሰስና የመስኖ ሥራ እንዲሁም ከእርሻ መሬት ልማት ጋር የተዛመዱ ሥራዎችን ማከናወን፣
- የተለያዩ የአዝእርት፣ የአትክልት፣ የፍራፍሬ እና የመሳሰሉትን ቅድመ መሥራች፣ መሥራችና የተመሰከረለት ዘር ማባዛት፣ ማበጠርና ማዘጋጀት፣ እንደ አስፈላጊነቱ ቅደመ መሥራች ዘሮችን ከውጭ ሀገር በማስመጣት ማስመረት ወይም መሸጥ፣ ተረፈ ምርቶችን ለገበያ ማቅረብ፣
- ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ሥራዎችን ማከናወን ናቸው፡፡

## 3.2 በኮርፖሬሽኑ የሚቀርቡ የግብርና ግብዓቶች እና አገልግሎቶች

- የግብርና ምርት ማሳደጊያዎችን (ማዳበሪያ፣ ምርጥ ዘር፣ አግሮ ኬሚካል ወዘተ) ገዝቶ ማከፋፈል፣

- የእርሻ መሣሪያዎችና መለዋወጫዎችን ገዝቶ ለሽያጭ ማቅረብ፣
- የተፈጥሮ ሙጫ ምርት መሰብሰብ፣ መግዛት እና እሴት በመጨመር ማዘጋጀት፣
- ከደን ውጤቶች የሚገኙ ምርቶችን በማምረትና በመሰብሰብ ለሀገር ውስጥ እና ለውጭ ሀገር ገበያ ማቅረብ፣
- የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት መስጠት፣
- የተለያዩ የአዝእርት፣ የአትክልት፣ የፍራፍሬ ቅድመ መሥራች፣ መሥራችና የተመሰከረለት ዘር ማባዛት፣ ማበጠርና ማዘጋጀት፣
- የእርሻ መሬት ልማት ሥራዎችን ማከናወን፣
- የእርሻ እና የኮንስትራክሽን መሣሪያዎች እንዲሁም የትራንስፖርት ተሽከርካሪዎች የኪራይ አገልግሎት መስጠት፣
- የጥገና፣ መገጣጠም፣ ማምረት እና የኢንጂነሪንግ ሥራዎችን ማካሄድ፣

## 3.3 የኮርፖሬሽኑ የሥራ ዘርፎች ምርት እና አገልግሎቶች

ኮርፖሬሽኑ በሚያቀርባቸው የግብርና ግብዓቶች እና ምርት ጥራት እና ዋጋ በደንበኞች ዘንድ ተቀባይነት በማግኘቱ በገበያ ውስጥ ጥሩ ተፎካካሪ መሆን ችሏል፡፡ ተቋሙ በእርሻ መሬት ልማት ሥራ፣ በሜካናይዜሽን፣ በእርሻ መሣሪያዎች አቅርቦት እንዲሁም በማዳበሪያ፣ አግሮ ኬሚካል፣ በምርጥ ዘር አቅርቦትና በደን ውጤቶች ምርት በመስኩ ካለው ሰፊ የገበያ ዕድል ውጤታማ ሆኖ መቀጠል የሚያስችል ዕድሎች አሉት፡፡

ከዚህ አኳያ በደንበኞች ዘንድ አመኔታና ተቀባይነት ያገኘባቸው የግብርና ግብዓቶች እና አገልግሎቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

### ሀ/ የምርጥ ዘር አቅርቦት

የምርጥ ዘር አቅርቦት የሥራ ዘርፍ የሚከተሉትን ሥራዎች ያከናውናል፣

- የእናት ዘር ከምርምር ተቋማት በመረከብ ደረጃ በደረጃ በራሱ የእርሻ መሬት በማባዛት እንዲሁም በአርሶ አደሩ ማሣ፣ በግልና በመንግሥት እርሻዎች በኮንትራት የተመሰከረለት ዘር ማምረት፣
- ለተጠቃሚዎች የሚቀርበው ዘር ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ እና የዘር አመራረት መስፈርቶችን ያሟላ መሆኑን በመስክና በላብራቶሪ የጥራት ቁጥጥር ማድረግ፣
- የዘር ተጠቃሚዎች የሚፈልጉትን የዘር አይነትና መጠን በተመጣጣኝ ዋጋ ዘሩ ከሚገኝበት ማዕከል በኮርፖሬሽኑ ትራንስፖርት ጭምር በማድረስ ማከፋፈል፣

- አዲስ ወደ ገበያ የሚገቡትን ዘሮች በገበሬዎች ማሣ፣ በሠርቶ ማሣያዎች እንዲሁም የአርሶ አደሮች ቀን በማዘጋጀት ማስተዋወቅ፣
- መስራች ዘሮችን በብዛት ማምረት እንዲሁም የኢኮኖሚ ጠቀሜታ ባላቸው የጥራጥሬ፣ የቅባትና የአትክልት ተፈላጊ ዘሮችን በማምረትና በማዘጋጀት ማቅረብ፣
- በተመረጡ ወረዳዎች ቀጥታ የዘር ሽያጭ ማከናወን ናቸው፡፡

## ለ/ የተቀናጀ የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት

የሥራ ዘርፉ የሚከተሉትን ሥራዎች ያከናውናል፣

- የእርሻ መሬት ልማት ጥናትና ዲዛይን፣ የእርሻ መሬት ቅየሳ፣ ምንጣሮና ማስተካከል፣ የውኃ ተፋሰስና የመስኖ ሥራ እንዲሁም ከእርሻ መሬት ልማት ጋር የተዛመዱ ሥራዎችን ማከናወን፣
- የማሣ ዝግጅት (እርሻ፣ ክስካሶ፣ ጥልቅ እርሻ፣ መስመር ማውጣት፣ ዘርና ማዳበሪያ መዝራት፣ ዘር ማልበስ)፣
- ምርት ስብሳቦ (አጭዶ ውቂያ፣ ቆሞ ውቂያ፣ በቆሎ መፈልፈል) እና
- ምርት የማጓጓዝ አገልግሎት ናቸው፡፡

## ሐ/ የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅርቦት

በዚህ ዘርፍ የምርት ማሳደጊያዎች ግብዓቶች የአቅርቦት አስተማማኝነት እንዲኖር እና ተገልጋዩ በዋጋ መናር እንዳይጐዳ ብሎም የዋጋ ማረጋጋት ሥራውን ትርጉም ባለው ደረጃ ለመስራት የሚቀርቡ ግብዓቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

- የተለያዩ ጠጣር የአፈር ማዳበሪያዎች (ዳፕ እና ዩሪያ)፣
- የተለያዩ ፈሳሽ ማዳበሪያዎች (ዉግዛል እና ባዮፌድ)
- የአበባ ማዳበሪያዎች (ፈሳሽና ጠጣር)፣
- አግሮ ኬሚካሎች፣
    - ፀረ-ነፍሳት (Inseticide)
    - ፀረ-አረም (Herbicide)
    - ፀረ-ሰብል (Fungicide)
    - የአይጥ መርዝ (Rodenticide)
- የኬሚካል መርጫ መሣሪያዎች፣
- የተለያዩ የጓሮ አትክልት እና የፍራፍሬ ዘር፣
- የእንስሳት መድኃኒቶችና የላብራቶሪ መገልገያዎች ናቸው፡፡

## መ/ የተፈጥሮ ሙጫና የደን ውጤቶች አቅርቦት፣

የሥራ ዘርፉ በማምረትና በግዥ የሚሰበስባቸው ምርቶች

- እጣን (Gum Olibanum)
- ከርቤ (Gum Myrrh)
- ሙጫ (Gum Arabic)
- አበከድ (Gum Oppoponax) ሲሆኑ፣ እነዚህ ምርቶች በደረጃ ተዘጋጅተው በዋናነት ለውጭ ሀገር ገበያ፣ በተወሰነ መጠንም ለሀገር ውስጥ ገበያ ይቀርባሉ፡፡

## ሠ/ የእርሻ መሣሪያዎች እና መለዋወጫዎች አቅርቦትና ሽያጭ

የሥራ ዘርፉ በዋነኝነት የሚያተኩረው የግብርና ምርታማነትን የሚያሳድጉ ቴክኖሎጂዎችን በመለየትና የተስማሚነት ፍተሻ በማድረግ ውጤታማነታቸው የተረጋገጠ የእርሻ መሣሪያዎችን፣ የኮንስትራክሽን መሣሪያዎችን፣ መለዋወጫዎችን ጎማዎችን ወዘተ ከውጭ ሀገር ገዝቶ ለሽያጭ ማቅረብ ነው፡፡

## ረ/ የተሽከርካሪዎች አስተዳደር እና ጥገና

የሥራ ዘርፉ በዋነኛነት የሚያተኩረው ከባድ ተሽከርካሪዎችን ማስተዳደር እንዲሁም የኪራይ እና የጥገና አገልግሎት መስጠት ናቸው፡፡

## ሸ/ የኢንጂነሪንግ፣ መገጣጠም እና ሥልጠና አገልግሎት

የሥራ ዘርፉ በዋነኛነት የሚያተኩረው ዘመናዊ የእርሻ መሣሪያዎችን፣ ተቀጽላዎችን የመፈብረክና መገጣጠም እንዲሁም የመሣሪያዎቹ አጠቃቀም እንዲለመድ አስፈላጊውን ሥልጠና መስጠት፣ ስለ እርሻ መሣሪያዎች አያያዝና አጠቃቀም የምክር አገልግሎት መስጠት፣ የቦሎ ምርመራ አገልግሎት መስጠት እንዲሁም የቴክኒክ ሞያ ሥልጠና መስጠት ናቸው፡፡

## 3.4 የደንበኞች መብቶች

- ሚስጥር ሆነው በሕግ እንዲጠበቁ ከተደነገጉት ውጭ ስለ ኮርፖሬሽኑ አጠቃላይ መረጃ በማግኘት ተጠቃሚ መሆን፣
- በቻርተሩ በተቀመጡት የአገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርድ እና በፍላጎታቸው መሠረት ምርት፣ ግብዓትና አገልግሎት የማግኘት መብት፣
- የአካል ጉዳተኞች፣ በዕድሜ የገፉ አረጋውያን እና ልዩ ትኩረት የሚሹ ተገልጋዮች በልዩ ትኩረት መስተናገድና አገልግሎት ማግኘት፣
- በቀረቡላቸው የግብርና ግብዓቶች እንዲሁም በተሰጣቸው አገልግሎት ላይ አስተያየት የመስጠት፣ ቅሬታ የማቅረብ፣ ላቀረቡት ቅሬታ ፍትሐዊ ምላሽ የማግኘት መብት፣

- ቅሬታቸውን በየደረጃው አቅርበው በቂ እና ወቅታዊ ምላሽ ባጡበት ጊዜ ለሌሎች ለሚመለከታቸው አካላት ማሳወቅ፣
- ወደ ኮርፖሬሽኑ አገልግሎት ፈልገው ሲመጡ በአግባቡ የመስተናገድ፣ እንዲሁም የአገልግሎት ሰጪውን ሠራተኛ ማንነትና የሥራ ድርሻ የማወቅ መብት አላቸው፡፡

## 3.5 የደንበኞች ግዴታዎች

- ትክክለኛ እና እውነተኛ ፍላጎታቸውን ማቅረብ፣
- ትክክለኛ እና ወቅታዊ መረጃዎችን የማዘጋጀትና የማቅረብ፣
- በራሳቸው ለፈጸሚቸው ጉድለቶችና ስህተቶች ባለቤት መሆን፣
- አድሎ፣ ኢ-ፍትሐዊ አሠራርና የተለየ ጥቅም ያለ መጠየቅ እና ያለማግኘት፣
- በጉቦ፣ በዝምድና፣ በጓደኝነት ለመጠቀም ያለመሞከር፣
- የሀገሪቱን ሕጎች፣ የኮርፖሬሽኑን ደንብና መመሪያዎች ማክበር ናቸው፡፡

## 3.6 የኮርፖሬሽኑ ሠራተኞች ለደንበኞች የገቡት ቃል

- በቻርተሩ በተቀመጠው ስታንዳርድ መሠረት የግብርና ግብአቶችን፣ የእርሻ መሣሪያዎችን እንዲሁም አገልግሎቶችን በጥራት፣ በወቅቱ እና በታማኝነት እናቀርባለን፣
- ቅድመ ሁኔታዎችን አሟልተው የሚመጡ ደንበኞችን ያለ አድሎ እና ወገናዊነት እናገለግላለን፣
- ለመርሆዎቻችንና እሴቶቻችን እንገዛለን፣
- የኮርፖሬት የሥነ-ምግባር መርሆዎችን ተግባራዊ እናደርጋለን፣
- ሀገራዊ የልማት ዕቅዶችን ለማሳካት በቁርጠኝነት ተግተን እንሰራለን፣
- ለተገልጋዮቻችን አስተያየቶች፣ ጥቆማዎችና ቅሬታዎች ትኩረት ሰጥተን መፍትሔ እንፈልጋለን፣
- የአቅርቦትና የአገልግሎት ብቃታችንን ከጊዜ ወደ ጊዜ በማሻሻል አቅማችንን በቀጣይነት ለመገንባት እንጥራለን፣
- ግልጽ እና ተጠያቂነት ያለው የአሠራር ሥርዓት እንዲኖር እናደርጋለን የሚሉት ናቸው፡፡

## 3.7 አስተያየትና ቅሬታ መቀበያ ዘዴዎች

ከደንበኞች የሚሰጠን አስተያየት፣ ጥቆማ፣ ጥያቄና ማብራሪያ ለአገልግሎታችን ጥራት መሻሻል አስተዋጽዖ ስላለው ደንበኞቻችን ለሚሰጡን አስተያየት ከፍተኛ ዋጋ እንሰጣለን፡፡ ግንኙነታችንን የበለጠ ለማጠናከር አገልግሎት አሰጣጣችንን በየዓመቱ የምናሻሽል ሲሆን፣ ከደንበኞች አስተያየትና ቅሬታ የምንቀበለው ከዚህ በታች በተዘረዘሩት መንገዶች ነው፡፡

- በኮርፖሬሽኑ ዋና መስሪያ ቤት በአካል በመገኘት ለሚመለከተው አካል በቃል ወይም በጽሁፍ ጥያቄ በማቅረብ፣
- በመስሪያ ቤቱ በሚገኙ አስተያየት መስጫ መዝገቦች እና ሳጥኖች
- በፋክስ፡- +251-114-42-13-12
- በመ.ሣ.ቁጥር፡- 6898
- በኢ.ሜይል፡- info@ethioagri.com or ethioagribusco@gmail.com
- በዌብ ሳይት፡- www.ethioagri.com
- በስልክ፡- +251-114-42-41-77/84 (ማዞሪያ)
- በፌስቡክ፡- Ethiopian Agricultural Businesses Corporation

## 3.8 የመረጃ ማስተላለፊያ ዘዴዎች

በኮርፖሬሽኑ በሚሰጡ አገልግሎቶች ላይ የተሟላ፣ ትክክለኛና ወቅታዊ መረጃዎችን ለሚመለከታቸው አካላት ለመስጠት የመረጃ ማሰራጫ ዘዴዎችን መምረጥና መጠቀም ይገባል፡፡ በዚህም መሠረት የኮርፖሬሽኑ የመረጃ ማስተላለፊያ ዘዴዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

- ኢ.ሜይል፡- info@ethioagri.com or ethioagribusco@gmail.com
- መ.ሣ.ቁጥር፡- 6898
- የማስታወቂያ ሰሌዳ
- ዌብ ሳይት፡- www.ethioagri.com
- መጽሔቶች እና ብሮሸሮች
- መገናኛ ብዙኀን (ሬዲዮ፣ ቴሌቪዥን) እና ጋዜጣ
- ማኅበራዊ ሚዲያ (ፌስቡክ፣ ቴሌግራም)

# ክፍል አራት

## 4. የቻርተሩ አተገባበር ሂደት

## 4.1 የቅሬታ አቀራረብ ሥርዓት

በቻርተሩ በተቀመጠው መሰረት አገልግሎት ያላገኘ ወይም በተሰጠው አገልግሎት ያልረካ ተገልጋይ ቅሬታ የማቅረብ መብት አለው። የቅሬታ አቀራረብና አፈታት ሥርዓቱም በሚከተለው አግባብ ይሆናል።

### ደረጃ አንድ
ደንበኛው ቅሬታውን በቀጥታ በቃል፣ በጽሁፍ፣ በስልክ፣ በመ.ሳ.ቁጥር፣ በፋክስና በኢ-ሜል ማቅረብ ይችላል።

### ደረጃ ሁለት
ቅሬታ የቀረበለት ፈጻሚ የቀረበለትን ቅሬታ አጣርቶ እንደ ክብደቱ መጠን እስከ ሁለት ሰዓት ባለው ጊዜ ውስጥ ተገቢውን ምላሽ መስጠት አለበት።

### ደረጃ ሦስት
በተሰጠው ምላሽ ያልረካ ደንበኛ ቀጥሎ ላለው ኃላፊ ቅሬታውን አቅርቦ ምላሽ ማግኘት ይችላል።

### ደረጃ አራት
በዚህ ሁኔታ የቀረበለት የሥራ ኃላፊም ቅሬታውን አጣርቶ እንደ ክብደቱ መጠን ከሁለት ሰዓት እስከ ሦስት ቀን ድረስ ምላሽ መስጠት አለበት።

### ደረጃ አምስት
አሁንም እርካታ ያላገኘ ደንበኛ ለተቋሙ የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍል አቅርቦ ምላሽ ማግኘት ይችላል። የሥራ ክፍሉም ሁኔታውን አጣርቶ እንደ ክብደቱ መጠን ከሁለት እስከ ሦስት የሥራ ቀናት መልስ ይሰጠዋል።

### ደረጃ ስድስት
በዚህ ያልረካ ደንበኛ ጉዳዩን ለኮርፖሬሽኑ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ማቅረብ ይችላል። ዋና ሥራ አስፈጻሚውም ቅሬታው እንዲጣራ በማድረግ ለቅሬታ አቅራቢው

በአምስት የሥራ ቀናት ውስጥ መልስ እንዲሰጠው ይደረጋል፡፡

### ደረጃ ሰባት

በመጨረሻም እነዚህን ደረጃዎች ተከትሎ ደንበኛው አሁንም በተሰጠው ውሳኔ ደስተኛ ካልሆነ ለሚመለከተው የመንግሥት አካል አቤቱታውን በማቅረብ መብቱን ማስከበር ይችላል፡፡

## 4.2 የክትትል እና የግምገማ ሥርዓት

የምንሰጣቸው አገልግሎቶች ስታንደርዳቸውን የጠበቁ እና የተገልጋዮችን እርካታ ያስገኙ እንዲሆኑ፡-

- ደንበኞች በቻርተሩ መሰረት አገልግሎት ስለማግኘታቸው በክትትልና ግምገማ ይረጋገጣል፣
- በየደረጃው ያሉ አመራሮች እና ፈጻሚዎች በቻርተሩ መሰረት አገልግሎት ስለመሰጠቱ በመገምገም ሪፖርታቸውን ለኮርፖሬሽኑ የበላይ አመራር ያቀርባሉ፣
- በሚቀርቡት የክትትል እና የግምገማ ሪፖርቶች ላይ በመመስረት የእርምትና የማስተካከያ እርምጃዎች ይወሰዳሉ፣
- የደንበኛ መድረኮች መደራጀታቸውና ሥራ ላይ መዋላቸው ይረጋግጣል፣
- በራስና በገለልተኛ ወገን የተገልጋዮች እርካታ ዳሰሳ መደረጉ ይጣራል፣
- የቅሬታ ማስተናገጃ ሥርዓት በአግባቡ መዘርጋቱ ይረጋገጣል፣
- በኮርፖሬሽኑ አሠራሮች እና ውሳኔዎቻችን ላይ ለሚቀርቡ የማብራሪያ ጥያቄዎች ተገቢው ማብራሪያ ለደንበኞች ይሰጣል፡፡

## 4.3 ተጠያቂነት

ማንኛውም በኢትዮጵያ የግብርና ሥራዎች ኮርፖሬሽን አገልግሎት የሚሰጥ አካል በዚህ የዜጐች ቻርተር የግብርና ቴክኖሎጂዎች የአቅርቦትና የአገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርድ መሰረት በቅንነትና በታማኝነት አገልግሎት የመስጠት ግዴታውን ያላከበረ እንደሆነ በኮርፖሬሽኑ የሥራ መሪያዎች መተዳደሪያ መመሪያ፣ በኅብረት ስምምነቱ እና በሌሎች አግባብነት ባላቸው መመሪያዎች መሰረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

## 4.4 የዜጐች ቻርተሩን በሥራ ላይ ስለማዋል

ቻርተሩ በሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ተገምግሞና በተገኙ ግብዓቶች ዳብሮ ይዘቱ የተሟላ በመሆኑ በኮርፖሬሽኑ የበላይ አመራር በሥራ ላይ እንዲውል ተደርጓል፡፡

## 4.5 የዜጐች ቻርተሩን ስለማሻሻል

ተቋማዊ የአደረጃጀት አሠራር ለውጥ ሲደረግ፣ እንዲሁም ከባለድርሻ አካላት እና ከደንበኞች ተገቢ እና አስፈላጊ የይሻሻል ጥያቄ ሲቀርብ እንዲሁም ይዘቱን ይበልጥ አዳብሮ ከወቅታዊ ሁኔታዎች ጋር ማጣጣም አስፈላጊ እና አስገዳጅ ሆኖ ሲገኝ ቻርተሩ ተከልሶ በበላይ አመራሩ ሲጸድቅ ሥራ ላይ የሚውል ይሆናል፡፡

# ክፍል አምስት

## 5. የአቅርቦት እና አገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርድ

## 5.1 የምርጥ ዘር አቅርቦት

| ተ.ቁ | የሚሰጡ አገልግሎቶች | አቅርቦቱ ወይም አገልግሎቱ የሚሰጥበት ዘርፍ | የአቅርቦት እና አገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርድ | | አቅርቦቱን እና አገልግሎቱን ለማግኘት የሚጠየቁ ቅድመ ሁኔታዎች |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | ጊዜ | የሚሰጥበት ሁኔታ | |
| 1 | የምርጥ ዘር አቅርቦት<br>1.1 የምርጥ ዘር ሽያጭ አገልግሎት መስጠት | የምርጥ ዘር አቅርቦት ዘርፍ | 5 - 10 ደቂቃ | በፅሁፍና በቃል | የዘር ዓይነትና ፍላጎት መለየት |
| | | | 10-30 ደቂቃ | በፅሁፍ | የዋጋና የባንክ አካውንት መስጠት |
| | | | ከ30 ደቂቃ-1 ሰዓት | በሰነድ | የባንክ ኢንቮይስ ሲመጣ ቼክ ማስደረግ |
| | | | ከ30 ደቂቃ-1 ሰዓት | በሰነድ | የሽያጭ ሰነድ ሰርቶ ለፋይናንስ አፈፃፀም ማህተም ማስደረግ፣ ለደንበኞችና ለቅርንጫፎች መላክ |
| | | | ከ1-2 ሰዓት | በፅሁፍ | ውለታ ማዘጋጀት፣ ማስፈረምና ለሚመለከተው በደብዳቤ መግለፅ |
| | 1.2 ለኮንትራት ዘር አባዦች ሥልጠና እና የሞያ ድጋፍ መስጠት | | 2 ሰዓት | በፅሁፍ | ስለ መሬት መረጣ ክላስተር መሆን |
| | | | 3 ሰዓት | በቪዲዮ የተደገፈ ሥልጠና | ስለ ሠብል እንክብካቤ በተመለከተ |
| | | | 2 ሰዓት | | ምርት አሰባሰብን በተመለከተ |
| | | | 3 ሰዓት | | የዘር ምርቱ በጥንቃቄ እንዴት መጓጓዝ እንዳለበት |
| | 1.3 የዘር ላቦራቶሪ የጥራት አገልግሎት ምርመራ መስጠት | | 12 ቀናት | በደብዳቤ፣ በፋክስ | ጥያቄ ማቅረብ |
| | 1.4 የምግብ እህል፣ ብጣሪ እና ሌሎች የሽያጭ አገልግሎት መስጠት | | እስከ 15 ቀናት | ጨረታ አየር ላይ የሚቆይበት ጊዜ | የጨረታ ሰነድ ግዥ |
| | | | እስከ 5 ቀናት | በፅሁፍ (በማስታወቂያ) | የጨረታ ውጤት ማሳወቅ |
| | | | እስከ 20 ቀናት | በፅሁፍ | የጨረታው አሸናፊ ክፍያ የሚፈፀምበት |
| | | | ከ30 ደቂቃ - 1 ሰዓት | በሰነድ | የባንክ ኢንቮይስ ሲመጣ ቼክ ማስደረግ |
| | | | 30 ደቂቃ | በሰነድ | የሽያጭ ሰነድ ሰርቶ ለፋይናንስ አፈፃፀም ማህተም በማስደረግ ለደንበኞችና ለቅርንጫፎች መላክ |
| | | | ከ1 - 2 ሰዓት | በፅሁፍ | ውለታ ማዘጋጀት፣ ማስፈረምና ለሚመለከተው በደብዳቤ መግለፅ |

18

# 5.2 የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት

| ተ.ቁ | የሚሰጡ አገልግሎቶች | አቅርቦቱ ወይም አገልግሎቱ የሚሰጥበት ዘርፍ | የአቅርቦት እና አገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርድ | | አቅርቦቱን እና አገልግሎቱን ለማግኘት የሚጠየቁ ቅድመ ሁኔታዎች |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | ጊዜ | የሚሰጥበት ሁኔታ | |
| | 1. የማሳ ዝግጅት አገልግሎት መስጠት | የግብርና ውጤቶች ሽያጭና የሜካናይዜሽን አገልግሎት ዘርፍ | - በመስክ ላይ እስከ 1 ሰዓት<br>- በኮንትራት የውጭ ስምምነት 3 ቀን | - ለመደበኛ አርሶ አደሮች በመስክ ላይ በቀጥታ ለሚቀርብ ጥያቄ በእጅ በእጅ ክፍያ የሚሡጥ ሲሆን፤<br>- ሠፋፊ ማሳ ላላቸው ባለሃብቶች የኮንትራት ውል ስምምነት በመፈጸም የሚከናወን ይሆናል፡፡ | አገልግሎቱን ለማግኘት ደንበኛው በአካል በመቅረብ ወይም በጽሁፍ ጥያቄ ማቅረብና በሚኖር የውል ስምምነት መሠረት ክፍያዎችን መፈጸም ይኖርበታል፤ |
| | 2. የምርት ስብሳቦና ማጓጓዝ አገልግሎት መስጠት | | - በመስክ ላይ እስከ 1 ሰዓት፣<br>- በኮንትራት የውጭ ስምምነት 3 ቀን | - ለመደበኛ አርሶ አደሮች በመስክ ላይ በቀጥታ ለሚቀርብ ጥያቄ እጅ በእጅ ክፍያ የሚሡጥ ሲሆን፤<br>- ሠፋፊ ማሳ ላላቸው ባለሃብቶች የኮንትራት ውል ስምምነት በመፈጸም የሚከናወን ይሆናል፡፡ | |
| | 3. የእርሻ መሣሪያዎች የኪራይ አገልግሎት መስጠት | | 1 ቀን | ከደንበኛው በሚቀርብ ጥያቄ መሠረት የውል ስምምነት በመፈራረምና ለሚፈለገው የኪራይ ሰዓት መጠን የቅድሚያ ክፍያ በመፈጸም የሚከናወን ይሆናል፡፡ | አገልግሎቱን ለማግኘት ደንበኛው በአካል በመቅረብ ወይም በጽሁፍ ጥያቄ ማቅረብ፣ የውል ስምምነት መፈጸምና የቅድሚያ ክፍያ መክፈል ይኖርበታል፤ |
| | 4. የእርሻ መሬት ልማት አገልግሎት መስጠት | | 15 ቀናት | የሥራ ቦታው አገልግሎቱን ለመስጠት ምቹ ስለመሆኑ በአካል በመገኘት በመገምገም ተቀባይነት ያለው ከሆነ የውል ስምምነት በመፈራረምና ለሚፈለገው የሥራ መጠን የቅድሚያ ክፍያ በመፈጸም የሚከናወን ይሆናል፡፡ | አገልግሎቱን ለማግኘት ደንበኛው በአካል በመቅረብ ወይም በጽሁፍ ጥያቄ ማቅረብ፣ የመሬት ይዞታ የባለቤትነት ማረጋገጫ ማስረጃ ማቅረብ እና የውል ስምምነት መፈጸምና የቅድሚያ ክፍያ መክፈል ይኖርበታል፤ |

# 5.3 የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅርቦት

| ተ.ቁ | የሚሰጡ አገልግሎቶች | አቅርቦቱ ወይም አገልግሎቱ የሚሰጥበት ዘርፍ | የአቅርቦት እና አገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርድ | | አቅርቦቱንና አገልግሎቱን ለማግኘት የሚጠየቁ ቅድመ ሁኔታዎች |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | ጊዜ | የሚሰጥበት ሁኔታ | |
| 1. | የጠጣር የአፈር ማዳበሪያ የሽያጭ አገልግሎት | የግብርና ግብዓት አቅርቦት ዘርፍ | ▪ 5 ደቂቃ | ▪ ለዘርፍ ሥራ አስፈጻሚ የቀረበ የደንበኛው የግዥ ጥያቄ ማመልከቻ ለሽያጭና ማርኬቲንግ መምሪያ መምራት፣ | ▪ ከግብርና ሚኒስቴር የአፈር ማዳበሪያ የግዥ ፈቃድ ደብዳቤ ያቀርባሉ፣ |
| | | | ▪ 10 ደቂቃ | ▪ የአፈር ማዳበሪያ ክምችት የሚገኝባቸውን ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች መረጃ የሽያጭና ማርኬቲንግ መምሪያ በማጣራት የደንበኛውን ፍላጎት ባማከለ ሁኔታ ደንበኛው ግዥ እንዲፈጽም ደብዳቤ ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ መላክ፣ | |
| | | | ▪ 1 ቀን | ▪ ደንበኛው በደብዳቤ ወደ ተላከበት ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በመሄድ ገንዘብ ወደ ባንክ ገቢ ካደረገ በኋላ እና በማግስቱ በቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ሲረጋገጥ የአፈር ማዳበሪያውን ይረከባል፣ | |
| 2. | የፈሳሽ ማዳበሪያ የሽያጭ አገልግሎት | | ▪ 5 ደቂቃ | ▪ የደንበኛው የግዥ ጥያቄ ማመልከቻ ለዘርፍ ሥራ አስፈጻሚ የቀረበ ከሆነ፣ የዘርፉ ሥራ አስፈጻሚ ለሽያጭና ማርኬቲንግ መምሪያ መምራት፣ | ▪ በአግሮ ኬሚካል ንግድ ሥራ ላይ የተሰማሩ ከሆነ የታደሰ የአግሮ ኬሚካል ንግድ ፈቃድ እና የግዥ ማመልከቻ ማሟላት፣<br>▪ በግብርና ኢንቨስትመንት ላይ የተሰማሩ ከሆነ የታደሰ የኢንቨስትመንት ፈቃድ፣ የመሬት ኪራይ ውልና ከወረዳ/ከዞን የድጋፍ ደብዳቤ የግዥ ማመልከቻ ማቅረብ፡፡<br>▪ የመንግሥት ተቋማት ከሆኑ ከተቋሙ ደብዳቤ ማፃፍ ይጠበቅባቸዋል፡፡ |
| | | | ▪ 10 ደቂቃ | ▪ የፈሳሽ ማዳበሪያ ክምችት የሚገኝባቸውን ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች መረጃ የሽያጭና ማርኬቲንግ መምሪያ በማጣራት የደንበኛውን ፍላጎት ባማከለ ሁኔታ ደንበኛው ግዥ እንዲፈጽም በደብዳቤ ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ መላክ፣ | |
| | | | ▪ 1 ቀን | ▪ ደንበኛው በደብዳቤ ወደ ተላከበት ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በመሄድ ገንዘብ ወደ ባንክ ገቢ ካደረገ በኋላ እና በማግስቱ በቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ሲረጋገጥ የፈሳሽ ማዳበሪያውን ይረከባል፣ | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 3. | የአግሮ ኬሚካል የሽያጭ አገልግሎት፣ | የግብርና ግብዓት አቅርቦት ዘርፍ | ▪ 5 ደቂቃ | ▪ የደንበኛው የግዥ ጥያቄ ማመልከቻ ለዘርፍ ሥራ አስፈጻሚ የቀረበ ከሆነ፤ የዘርፉ ሥራ አስፈጻሚ ለሽያጭና ማርኬቲንግ መምሪያ መምራት፣ | ▪ በአግሮ ኬሚካል ንግድ ሥራ ላይ የተሰማሩ ከሆነ የታደሰ የአግሮ ኬሚካል ንግድ ፈቃድ እና የግዥ ማመልከቻ ማሟላት፤<br>▪ በግብርና ኢንቨስትመንት ላይ የተሰማሩ ከሆነ የታደሰ የኢንቨስትመንት ፈቃድ፣ የመሬት ኪራይ ውልና ከወረዳ/ከዞን የድጋፍ ደብዳቤ እንዲሁም የግዥ ጥያቄ ማመልከቻ ማቅረብ፣<br>▪ የመንግሥት ተቋማት ከሆኑ ከተቋሙ ደብዳቤ ማስፃፍ ይጠበቅባቸዋል፡፡ |
| | | | ▪ 10 ደቂቃ | ▪ የአግሮ ኬሚካሉ ክምችት የሚገኝባቸውን ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች መረጃ የሽያጭና ማርኬቲንግ መምሪያ በማጣራት የደንበኛውን ፍላጎት ባማከለ ሁኔታ ደንበኛው ግዥ እንዲፈጽም በደብዳቤ ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ መላክ፣ | |
| | | | ▪ 1 ቀን | ▪ ደንበኛው በደብዳቤ ወደ ተላከበት ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በመሄድ ገንዘብ ወደ ባንክ ገቢ ካደረገ በኋላ እና በማግስቱ በቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ሲረጋገጥ አግሮ ኬሚካሉን ይረከባል፣ | |
| 4. | የኬሚካል መርጫ መሣሪያ የሽያጭ አገልግሎት፣ | የግብርና ግብዓት አቅርቦት ዘርፍ | ▪ 5 ደቂቃ | ▪ የደንበኛው የግዥ ጥያቄ ማመልከቻ ለዘርፍ ሥራ አስፈጻሚ የቀረበ ከሆነ፤ የዘርፉ ሥራ አስፈጻሚ ለሽያጭና ማርኬቲንግ መምሪያ መምራት፣ | ▪ በአግሮ ኬሚካል ንግድ ሥራ ላይ የተሰማሩ ከሆነ የታደሰ የአግሮ ኬሚካል ንግድ ፈቃድ እና የግዥ ማመልከቻ ማሟላት፤<br>▪ በግብርና ኢንቨስትመንት ላይ የተሰማሩ ከሆነ የታደሰ የኢንቨስትመንት ፈቃድ፣ የመሬት ኪራይ ውልና ከወረዳ/ከዞን የድጋፍ ደብዳቤ እንዲሁም የግዥ ጥያቄ ማመልከቻ ማቅረብ፣<br>▪ የመንግሥት ተቋማት ከሆኑ ከተቋሙ ደብዳቤ ማስፃፍ ይጠበቅባቸዋል፡፡ |
| | | | ▪ 10 ደቂቃ | ▪ የመርጫ መሣሪያ ክምችት የሚገኝባቸውን ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች መረጃ የሽያጭና ማርኬቲንግ መምሪያ በማጣራት የደንበኛውን ፍላጎት ባማከለ ሁኔታ ደንበኛው ግዥ እንዲፈጽም በደብዳቤ ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ መላክ፣ | |
| | | | ▪ 1 ቀን | ▪ ደንበኛው በደብዳቤ ወደ ተላከበት ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በመሄድ ገንዘብ ወደ ባንክ ገቢ ካደረገ በኋላ እና በማግስቱ በቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ሲረጋገጥ የመርጫ መሣሪያውን ይረከባል፤ | |
| 5. | የእንስሳት መድሃኒት የሽያጭ አገልግሎት፣ | የግብርና ግብዓት አቅርቦት ዘርፍ | ▪ 5 ደቂቃ | ▪ የደንበኛው የግዥ ጥያቄ ማመልከቻ ለዘርፍ ሥራ አስፈጻሚ የቀረበ ከሆነ፤ የዘርፉ ሥራ አስፈጻሚ ለሽያጭና ማርኬቲንግ መምሪያ መምራት፣ | ▪ የግዥ ጥያቄ ማመልከቻ ማቅረብ፣<br>▪ ከእንስሳት መድሃኒትና መኖ አስተዳደር ቁጥጥር ባለስልጣን የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ (ለዓመቱ የታደሰ) ማቅረብ፣<br>▪ የታደሰ የእንስሳት መድሃኒት ጅምላ ሽያጭ ንግድ ፈቃድ፣<br>▪ መድሃኒቶቹን ለመግዛት ሲመጡ የድርጅታቸውን ክብ ማህተም ይዘው መቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡ |
| | | | ▪ 10 ደቂቃ | ▪ የእንስሳት መድሃኒት ክምችት የሚገኝባቸውን ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች መረጃ የሽያጭና ማርኬቲንግ መምሪያ በማጣራት የደንበኛውን ፍላጎት ባማከለ ሁኔታ ደንበኛው ግዥ እንዲፈጽም በደብዳቤ ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ መላክ፣ | |
| | | | ▪ 1 ቀን | 22<br>▪ ደንበኛው በደብዳቤ ወደ ተላከበት ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በመሄድ ገንዘብ ወደ ባንክ ገቢ ካደረገ በኋላ እና በማግስቱ በቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ሲረጋገጥ የእንስሳት መድሃኒቱን ይረከባል፣ | |

## 5.5 የእርሻ መሣሪያዎች እና መለዋወጫዎች አቅርቦትና ሽያጭ

| ተ.ቁ | የሚሰጡ አገልግሎቶች | አቅርቦቱ ወይም አገልግሎቱ የሚሰጥበት ዘርፍ | የአቅርቦት እና አገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርድ | | አቅርቦቱን እና አገልግሎቱን ለማግኘት የሚጠየቁ ቅድመ ሁኔታዎች |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | ጊዜ | የሚሰጥበት ሁኔታ | |
| 1 | የእርሻ መሣሪያዎች እና መለዋወጫዎች አቅርቦትና ሽያጭ | የእርሻ መሣሪያዎች አቅርቦት ዘርፍ | 30 ደቂቃ | - በአካል<br>- በስልክ<br>- በኢ-ሜል | - ጥያቄ ማቅረብ<br>- ክፍያ መፈጸም<br>- ንብረቶችን መረከብ |
| | 1.1 የቀጥታ ሽያጭ አገልግሎት መስጠት | | | | |
| | 1.2 የጨረታ ሽያጭ አገልግሎት መስጠት | | 14 ሰዓት | - በጽሑፍ | - የጨረታ ማስታወቂያ ማውጣት<br>- የጨረታ ሰነድ ማዘጋጀት<br>- ጨረታ መክፈት<br>- ውል መዋዋል<br>- ቅድመ ክፍያ መክፈል<br>- ንብረት መረከብ |
| | 1.3 የሽያጭ ዕቃዎች አቅርቦት አገልግሎት መስጠት | | 90 ደቂቃ | - በጽሑፍ | - ጥያቄ ማቅረብ<br>- የውጭ ምንዛሬ ፈቃድ ማግኘት<br>- የጭነት ክትትል ማድረግ<br>- የክሊራንስ ሥራዎች መስራት |
| | 1.4 የገበያ ፍላጎትና የማስተዋወቅ አገልግሎት መስጠት | | 64 ሰዓት | - በአካል<br>- በጽሑፍ | ---- |

## 5.6 የከባድ ተሽከርካሪዎች ኪራይና ጥገና

| ተ.ቁ | የሚሰጡ አገልግሎቶች | አቅርቦቱ እና የሚሰጥበት ዘርፍ/አገልግሎት | የአቅርቦት እና አገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርድ | | አቅርቦቱን እና አገልግሎቱን ለማግኘት የሚጠየቁ ቅድመ ሁኔታዎች |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | ጊዜ | የሚሰጥበት ሁኔታ | |
| 1 | የጥገና አገልግሎት በመስክና በጋራዥ ውስጥ መስጠት | የተሽከርካሪዎች አስተዳደርና ጥገና ዘርፍ | ➢ ቀላል ጥገና 1-3 ቀን<br>➢ ከባድ ጥገና 4-20 ቀን | ➢በደብዳቤ በሚቀርብ ጥያቄ<br>➢ጨረታ በመሳተፍ | -የጥገና ሥራ ትዕዛዝ በመክፈት (ለውስጥ)<br>- ለውጪ ደንበኞች ከሆነ መጀመሪያ ውል መዋዋል እና የሥራ ትዕዛዝ መክፈት |
| 2 | የከባድ ተሽከርካሪዎች አገልግሎት መስጠት | | ቅድመ ሁኔታ ከተሟላ 1ቀን | ➢በደብዳቤ በሚቀርብ ጥያቄ<br>➢ጨረታ በመሳተፍ<br>➢በስልክ እና በተለያዩ መገናኛ ዘዴዎች በሚቀርብ ጥያቄ | -በዋጋ መስማማት እና ውል መፈራረም |
| 3 | ያገለገሉ ተሽከርካሪዎችን፣ መሣሪያዎችንና ንብረቶችን ማስወገድ | | በጨረታ ማሸነፉ ከተረጋገጠ በ10 ቀናት | ➢ጨረታ በማውጣት | -ሕጋዊ መስፈርት አሟልቶ በጨረታ መሳተፍ |

# 5.7 ኢንጂነሪንግ፣ መገጣጠም እና ሥልጠና

| ተ.ቁ | የሚሰጡ አገልግሎቶች | አገልግሎቱ የሚሰጥበት የሥራ አመራር | የአቅርቦት እና አገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርድ | | አቅርቦቱን እና አገልግሎቱን ለማግኘት የሚጠየቁ ቅድመ ሁኔታዎች |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | ጊዜ | የሚሰጥበት ሁኔታ | |
| 1 | የእርሻ መሣሪያዎችን ተቀጽላዎችን የመፈብረክና የመገጣጠም ሥራ | የእርሻ መሣሪያዎች አቅርቦት ዘርፍ | ከ5 - 45 ቀን | ከደንበኛው የቀረበን ጥያቄ ለማስተናገድ የሚቻል ስለመሆኑ በማጣራትና ለአገልግሎቱ በሚያስፈልግ የክፍያ መጠን ላይ ስምምነት በመድረስ የሚከናወን ይሆናል፡፡ | አገልግሎቱን ለማግኘት ደንበኛው በአካል በመቅረብ ወይም በጽሁፍ ጥያቄ ማቅረብ፣ የውል ስምምነት መፈጸምና የቅድሚያ ክፍያ መክፈል ይኖርበታል፤ |
| 2 | የሥልጠና አገልግሎት በመስክና በማሠልጠኛ ማዕከል መስጠት | | ከ1 - 3 ቀን | | |

# 5.8 የመረጃ አገልግሎት መስጠት

| ተ.ቁ | የሚሰጡ አገልግሎቶች | አገልግሎቱ የሚሰጥበት የሥራ አመራር | የአቅርቦት እና አገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርድ | | አቅርቦቱን እና አገልግሎቱን ለማግኘት የሚጠየቁ ቅድመ ሁኔታዎች |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | ጊዜ | የሚሰጥበት ሁኔታ | |
| 1 | ለመረጃ ፈላጊ አካላት አስፈላጊውን መረጃ አዘጋጅቶ መስጠት | ዘርፎች፣ የሥራ አመራሮች፣ መምሪያዎች ቅርንጫፎች እና ማዕከሎች | ከ30 ደቂቃ እስከ 3 ቀናት | በስልክ<br>በአካል<br>በጽሁፍ<br>በኢሜል | ጥያቄ ማቅረብ |
| 2 | ወርሃዊ፣ የሩብ ዓመት፣ የግማሽ ዓመት እና ዓመታዊ ሪፖርቶችን ማቅረብ | | -ወርሃዊ ለውስጥ ወር በገባ በ5 ቀናት እና ለውጪ ከ10 ቀናት በኋላ<br>-የሩብ ዓመት ለውስጥ ወር በገባ ከ10 እና ለውጪ ከ15 ቀናት በኋላ<br>-ዓመታዊ ለውስጥ ወር በገባ 20 ቀናት እና ለውጪ ከ25 ቀናት በኋላ | በሶፍት ኮፒ(E-mail,Telegram,Flash,etc,) | - ጥያቄ ማቅረብ |
| 3 | በተሰጡ አገልግሎቶች ከደንበኞች የሚቀርቡ ቅሬታዎችን አጣርቶ ወቅታዊ እና ተገቢ ምላሽ መስጠት | | ቅሬታ በቀረበ በአምስት የሥራ ቀናት ውስጥ | በስልክ<br>በአካል<br>በጽሁፍ | በአካል፣ በጽሁፍ ወይም በቃል ቅሬታ በማቅረብ |
| 4 | የኮርፖሬሽኑ የፋይናንስ መረጃን በዓመታዊ መጽሔት (Disclosure Magazine) ለኅብረተሰቡ ማሳወቅ | | የተዘጋ ዓመታዊ ሂሳብ ሪፖርት በቀረበ በ1 ወር ውስጥ | በጽሁፍ<br>(በሕትመት) | - ጥያቄ ማቅረብ |

# ክፍል ስድስት

## 6. ተቋማዊ መዋቅር

የኢትዮጵያ የግብርና ሥራዎች ኮርፖሬሽን ተጠሪነቱ ለኢትዮጵያ የኢንቨስትመንት ሆልዲንግስ ሲሆን፣ በሥራ አመራር ቦርድ ይመራል፡፡ ኮርፖሬሽኑ በመንግሥት የተሰጠውን ተልዕኮ ከመወጣት አኳያ በአራት ኮርፖሬት ዘርፎች፣ ዓላማ አስፈፃሚ በሆኑ አምስት የኦፐሬሽን ዘርፎች፣ በ14 ድጋፍ ሰጪ የሥራ ሂደቶች እንዲሁም በ25 ቅርንጫፎች እና ጣቢያዎች በተደራጀ መዋቅር ግብርናን ለማዘመን እየሰራ ይገኛል፡፡

## የኢትዮጵያ የግብርና ሥራዎች ኮርፖሬሽን ተቋማዊ መዋቅር



# የኢትዮጵያ የግብርና ሥራዎች ኮርፖሬሽን (ኢግሥኮ) አድራሻ

አዲስ አበባ ወደ ቃሊቲ በሚወስደው መንገድ ከኢኳቴሪያል ቢዝነስ ግሩፕ ዝቅ ብሎ አልያም ከፋፋ ምግብ አ/ማ 150 ሜትር ወደ ውስጥ ገባ ብሎ ይገኛል፡፡
ስልክ፡- +251-114 42 41 77/84 (ማዞሪያ)
ዋና ሥራ አስፈጻሚ ቢሮ፡- +251-114 42 26 79

## አዘጋጅ

ኮርፖሬት ኮሚዩኒኬሽን እና ማኅበራዊ ኃላፊነት ሥራ አመራር
+251-114 42 41 25
ፋክስ፡- +251-114 42 13 12
የመ.ሣ.ቁጥር:- 6898
ኢ-ሜይል፡- info@ethioagri.com or ethioagribusco@gmail.com
ዌብ ሳይት፡- www.ethioagri.com
ፌስቡክ፡- Ethiopian Agricultural Businesses Corporation

የምርጥ ዘር አቅርቦት ዘርፍ
ስልክ፡- +251-11-661-2266
ፋክስ፡- +251-11- 618- 6123

የግብርና ግብዓት አቅርቦት ዘርፍ
ስልክ፡- +251-11-442-5623/28
ፋክስ፡- +251-11-442-5622

የእርሻ መሣሪያዎች አቅርቦት ዘርፍ
ስልክ፡- +251-11-442-3438
ፋክስ፡- +251-11-442-0895

የተሽከርካሪዎች አስተዳደርና ጥገና ዘርፍ
ስልክ፡- +251-11-470-8470
ፋክስ፡- +251-11-442-0434

የግብርና ውጤቶች ሽያጭና ሜካናይዜሽን አገልግሎት ዘርፍ
ስልክ፡- 0114 42 50 12

የኮርፖሬት ሀብት አመራር ዘርፍ
ስልክ፡- +251-11-442-1213
ፋክስ፡- +251-11-442-2314

ግብርናን ማዘመን ግባችን ነው!

የኢትዮጵያ የግብርና ሥራዎች ኮርፖሬሽን
ETHIOPIAN AGRICULTURAL BUSINESSES CORPORATION

የደንበኞቻችንን ፍላጎት ለማሟላት
በትጋት እንሠራለን!